# የተፈቀደለት ተወካይ ማረጋገጫ ዝርዝር

ይህን ማረጋገጫ ዝርዝር ስለተፈቀደለት ተወካይ ሁኔታ ለማመልከት ለመዘጋጀት ይጠቀሙት።

አንድ ይግባኝ ባይ እሱን ወክሎ የሚሰራ የተፈቀደለት ተወካይ ሊኖረው ይችላል። የይግባኝ ባይ የተፈቀደለት ተወካይ ለመሆን ከማመልከትዎ በፊት ስለ ተወካዮች አይነቶች እና ስለሚያስፈልጉዎት ሰነዶች ለማወቅ የተፈቀደለት ወኪል ዝርዝር ማስረጃ ቅጽን እና በይግባኝ ባይ የተመደበ ተወካይ ዝርዝር ማስረጃ ቅጽን ይመልከቱ።

## ይዘጋጁ

**ከማመልከትዎ በፊት:**

በአንድ ጊዜ ለአንድ ይግባኝ ባይ እውቅና የምንሰጠው ለአንድ ተወካይ ብቻ ነው።

## ደረጃ 1: የሚሞሉትን ትክክለኛ መርሀግብር ይምረጡ

እርስዎ ይግባኝ ባይ ከሆኑ በየሕግባኝ ባይ የተመደበ ተወካይ ቅጽን በመሙላት አንድን ሰው ተወካይዎ አድርገው መመደብ ይችላሉ።

አንድን ይግባኝ ባይ በራሱ ተወካይ መመደብ የማይችል በመሆኑ ምክንያት ለመወከል ከፈለጉ ከሚከተሉት መርሀግብሮች መካከል አንዱን ይምረጡ፡

- የመወሰን ችሎታ የሌለው ይግባኝ ባይ የተፈቀደለት ወኪል መርሀግብር
- የሟች ይግባኝ ባይ የተፈቀደለት ወኪል መርሀግብር

እነዚህ መርሀግብሮች የተፈቀደለት ወኪል ለመሆን የሚያስፈልጉዎትን ቅጾች ይይዛሉ። መርሀግብሮቹ በተጨማሪም ጠቃሚ ሆነው ሊያገኟቸው የሚችሏቸውን ተጨማሪ ቅጾች ይይዛሉ። ሁለቱንም መርሀግብሮች ከድረገጻችን ላይ ያገኟቸዋል።

**ማስታወሻ:** በህግ ክርክር አማካኝነት የተሾሙ የተፈቀደለት ተወካይ ከሆኑ ይህን ደረጃ ይለፉት። የህግ ስልጣንዎን የሚያረጋግጥ ኦፊሴላዊ፣ በፍርድ ቤት የተሰጠ ሰነድ ለእኛ መላክ አለብዎ። በተጨማሪም ማንነትዎን ማረጋገጥ ይጠበቅብዎታል። ይህን እንዴት እንደሚያደርጉ በተመለከተ ከታች የቀረበውን መረጃ ይመልከቱ።

## ደረጃ 2: ሰነዶች ይሰብስቡ

ከተሞላው ቅጽዎ ጋር መላክ የሚኖርብዎ **ሶስት** አይነት ሰነዶች አሉ።

1. **የቤተሰብ ዝምድናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች**
   **(**ለተፈቀደላቸው ወኪሎች ብቻ ተፈጻሚ ይሆናሉ**)**

   አንድ ይግባኝ ባይ ጉዳዮቹን የሚስተዳድርለት የውክልና ስልጣን ያለው ሰው ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ ተወካይ ከሌለው የሚከፈልበት እረፍት የተፈቀደለት ወኪል ይፈቅዳል። ይህ ሰው የመወሰን ችሎታ የሌላቸው ወይም ህይወታቸው ያለፈ ይግባኝ ባዮችን ወክሎ ሊሰራ ይችላል። ሆኖም ተወካዩ ከይግባኝ ባዩ ጋር ያለውን ዝምድና ማረጋገጥ አለበት።

   ከይግባኝ ባዩ ጋር ያለውን ዝምድና ለማረጋገጥ አንድ **የመወሰን ችሎታ የሌለው ይግባኝ ባይ የተፈቀደለት ወኪል** ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ማቅረብ አለበት**:**

   - የተረጋገጠ የቤት ውስጥ አናናሪነት መግለጫ

- ሕጋዊ የልደት ማስረጃ
- ሕጋዊ የጋብቻ ማስረጃ
- በኦሬጎን የሚከፈልበት እረፍት **(Paid Leave Oregon)** ውሳኔ በገለልተኛ ሶስተኛ ወገን የተሰጡ በይግባኝ ባይ እና የይግባኝ ባዩ ተወካይ ሆኖ ለመስራት በሚያመለክተው ሰው መካከል ያለውን የጋብቻ፣ የቤት ውስጥ አኗኗሪነት፣ የወላጅነት ወይም ሌላ የቤተሰብ ዝምድና የሚረጋግጡ ሌሎች ሰነዶች።

ከይግባኝ ባይ ጋር ያለውን ዝምድና ለማረጋገጥ አንድ **የሟች ይግባኝ ባይ የተፈቀደለት ወኪል** ከሚከተሉት ውስጥ አንዱን ማቅረብ አለበት**:**

- ሕጋዊ የልደት ማስረጃ
- ሕጋዊ የጋብቻ ማስረጃ
- በኦሬጎን የሚከፈልበት እረፍት **(Paid Leave Oregon)** ውሳኔ በገለልተኛ ሶስተኛ ወገን የተሰጡ በይግባኝ ባይ እና የይግባኝ ባዩ የተፈቀደለት ወኪል ሆኖ ለመስራት በሚያመለክተው ሰው መካከል ያለውን የጋብቻ፣ የወላጅነት ወይም ሌላ የቤተሰብ ዝምድና የሚረጋግጡ ሌሎች ሰነዶች።
- ባለአደራ መሆንዎን የሚያረጋግጥ የባለ አደራነት ሰነድ።

ሰነድዎ እነዚህን መስፈርቶች ስለማሟላቱ እርግጠኛ ካልሆኑ እባክዎ ለሚከፈልበት እረፍት በስልክ ቁጥር **833-854-0166** ይደውሉ።

**2. የይግባኝ ባዩን እና ይግባኝ ባዩን ለመወከል የሚያመለክተውን ሰው ማንነት የሚያረጋግጡ ተቀባይነት ያላቸው ሰነዶች** **(**በይግባኝ ባይ ለተመደቡ ተወካዮች ተፈጻሚ አይሆንም**)**

- ለራስዎ ተወካይ የሚመድቡ ከሆነ የእርስዎን ማንነት ማረጋገጫ ሰነዶችን በድጋሚ መላክ አይጠበቅብዎትም።
- የተፈቀደለት ወኪል ለመሆን በሚያመለክቱበት ጊዜ ማንነትዎን እና የይግባኝ ባዩን ማንነት የሚያረጋግጡ ሰነዶችን ማቅረብ አለብዎ። ለእርስዎ እና ለይግባኝ ባዩ ሁለት የመጀመሪያ ደረጃ የማንነት ማረጋገጫ ሰነዶች ከለር ኮፒዎችን ወይም አንድ የመጀመሪያ ደረጃ እና ሁለት ሁለተኛ ደረጃ የማንነት ማረጋገጫ ሰነዶችን ለእኛ መላክ አለብዎ።

### የመጀመሪያ ደረጃ ሰነዶች

- በዩኤስ መንግስት ወይም ግዛት የተሰጠ የመንጃ ፍቃድ **(**ወይም የተማሪ ፍቃድ**)** **(**የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበትን ፍቃድ የአገልግሎት ጊዜው ያበቃው ባለፉት **12** ወራት ውስጥ ከሆነና ተከታታይ ከሆነ እንቀበላለን**)**።
- ሌላ በመንግስት የተሰጠ ፎቶ ያለበት መታወቂያ **(**ከነ ፎቶው ቋሚ ሰነድ መሆን አለበት። የሚሊተሪ መታወቂያዎች፣ ጊዜያዊ ወይም የወረቀት ሰነዶች ተቀባይነት የላቸውም**)**።
- በግዛት የተሰጠ ፎቶ ያለበት መታወቂያ **(**የአገልግሎት ጊዜው ያለፈበትን መታወቂያ የአገልግሎት ጊዜው ያበቃው ባለፉት **12** ወራት ውስጥ ከሆነና ተከታታይ ከሆነ እንቀበላለን**)**።
- የዘማች የጤና መታወቂያ ካርድ
- የ**DHS** ታማኝ ተጓዦች ካርዶች **(Global Entry፣ NEXUS፣ SENTRI)**
- የካናዳ የመንጃ ፍቃድ
- በነዋሪነት ዜግነት ማግኛ የምስክር ወረቀት **(**ቅጽ **N-550** ወይም **N-570)**
- ብሔራዊ መታወቂያ ካርድ **(**ከዩኤስ ውጭ ነዋሪ ከሆኑ ብቻ**)**
- በፌደራል እውቅና የተሰጠው፣ በጎሳ የተሰጠ ፎቶ ያለበት መታወቂያ
- በዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት የተሰጠ የስደተኛ ያልሆነ

- የዩኤስ ፓስፖርት ወይም የዩኤስ ፓስፖርት ካርድ
- የዩ.ኤስ የቋ ነዋሪነት ካርድ **(I-551**
- በዩኤስሲአይኤስ/**USCIS**-የተሰጠ የስራ ቅጥር ፍቃድ ካርድ **(I-766)** (በአሰሪ የተሰጡ መታወቂያ ካርዶች ተቀባይነት የላቸውም)
- የውጭ አገር ፓስፖርት

ቪዛ (የአገልግሎት ጊዜው ከአምስት ዓመታት በላይ ያላለፈበት)

በዩኤስ ስቴት ዲፓርትመንት የተሰጠ ጊዜያዊ የስደተኛ ቪዛ **(I551)** (የአገልግሎት ጊዜው ከአምስት ዓመታት በላይ ያላለፈበት)

**ሁለተኛ ደረጃ ሰነዶች** (የሚከተሉት ሰነዶች ሙሉ ከለር ስካኖች እና ፒዲኤፎች እንደ ሁለተኛ ደረጃ ሰነዶች ተቀባይነት አላቸው)

- የማህበራዊ ዋስትና ካርድ
- የዩኤስ የውጭ አገር ውልደት (ልደት) ማረጋገጫ **(FS-545)**
- የዩኤስ የውልደት (ልደት) ሪፖርት ማረጋገጫ **(DS-1350)**
- የዩኤስ ቆንስላ የውጭ አገር ውልደት (ልደት) ሪፖርት **(FS-240)**
- የዩኤስ የጤና መድን ዋስትና ካርድ
- ህጋዊ ማህተም የተመታበት የዩኤስ የልደት ማስረጃ (የመጀመሪያና የመጨረሻ ስም)
- **W-2** ቅጽ
- **1098** ቅጽ
- የመኪና መድን ዋስትና ካርድ
- የድንበር ማቋረጫ ካርድ
- የዩኤስ የወደብ ዘብ የነጋዴ መርከበኛ ካርድ
- የዩኤስ ዜጋ የመታወቂያ ካርድ ቅጽ **(I-197)**
- የካናዳ ህንዳውያን የሰሜን ጉዳዮች ካርድ
- የኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ ፎቶ ያለበት መታወቂያ
- የኮሌጅ ወይም ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ማስረጃ /ትራንስክሪፕት/
- የ**DOD** መልቀቂያ ማረጋገጫ
- የመኪና ወይም የቤት መድን ዋስትና መግለጫ
- የነዋሪነት ማረጋገጫ ደብዳቤ
- የተጨማሪ ምግብ ድጎማ ፕሮግራም ተቀባይነት ማረጋገጫ
- የነባር አሜሪካዊ ጎሳ ሰነድ
- የ**SSA-1099** ያልሆነ ቅጽ
- የ**SSA-1099** ቅጽ
- የዩኤስ ወይም የዩኤስ ግዛት የመራጭ ምዝገባ ካርድ ወይም የምስክር ወረቀት
- የሴቶች፣ ጨቅላ ህጻናት እና ህጻናት **(WIC)** የፖርቶሪኮ የተቀባይ ማረጋገጫ

**ሁለተኛ ደረጃ ሰነዶች** (ከተሰጡ ከ**90** ቀናት በታች የሆኑ)

- **የአገልግሎት ክፍያ** (የሂሳብ ቁጥርዎን፣ ሙሉ ስምዎን፣ እና ወቅታዊ አድራሻዎን የሚያሳይ)
- **የህክምና ክፍያ** (የሂሳብ ቁጥርዎን፣ ሙሉ ስምዎን፣ እና ወቅታዊ አድራሻዎን የሚያሳይ)
- **የባንክ፣ የብድር ወይም የፋይናንስ ተቋም መግለጫ** (የሂሳብ ቁጥርዎን፣ ሙሉ ስምዎን፣ እና ወቅታዊ አድራሻዎን የሚያሳይ፤ በባንክ የተሰጠ)
- **የክፍያ ጉራጅ** (ሙሉ ስምዎን፣ የአሰሪ ወይም ኩባንያ ስም፣ ወቅታዊ አድራሻዎን የሚሳይ፤ የክፍያ ቼክ ሳይሆን ትክክለኛ የክፍያ ጉራጅ መሆን አለበት)

**3. የይግባኝ ባይን ሁኔታ የሚያረጋግጥ ሰነድ**

- የመወሰን ችሎታ የሌለው ሰው **የተፈቀደለት ወኪል ለመሆን የሚያመለክት ሰው** የይግባኝ ባዩ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ይግባኝ ባዩ የመወሰን ችሎታ እንደሌለው እንዲያረጋግጥ ማድረግ አለበት። አቅራቢው የመወሰን ችሎታ ለሌለው ይግባኝ ባይ ቅጽ የተፈቀደለት ወኪል ክፍል **E**ን ሊሞላ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መረጃ የያዘ ሰነድ ሊያቀርብ ይችላል።

  **ማስታወሻ:** ይግባኝ ባዩን የሚወክሉት በውክልና ስልጣን ከሆነ ወይም ይግባኝ ባዩን እንዲወክሉ በፍርድ ቤት ከተሾሙ ይህን ሰነድ መላክ አይጠበቅብዎትም።

- የሟች ይግባኝ ባይ **የተፈቀደለት ወኪል ለመሆን የሚያመለክተው ሰው** የሞቱን ቀን የሚያረጋግጥ የሞት ማስረጃ ወይም ሌላ ሰነድ መላክ ይጠበቅበታል (በመምሪያው የተፈቀደ)።

## ደረጃ 3: ሰነዶችዎን ይላኩ

ቅጽዎን እና የማረጋገጫ ሰነዶችዎን መላክ ይችላሉ:

- እንደ የእኛ ያነጋግሩን ቅጽ አባሪዎች
- ሰነዶችዎን ለሚከተለው በመልዕክት ይላኩ:

**Attn: Paid Leave Oregon**
**Oregon Employment Department**
**875 Union St. NE**
**Salem, OR 97311**